Amharic Translation

## የ2018 የአለም ቴአትር ቀን የአውሮፓ መልዕክት

## ሲሞን ማክበርኒ ከእንግሊዝ

## ተዋናይ፣ጸሐፌተውኔት፣መራሔተውኔት እና የቴአትር ዴ ኮምሊሲቴ

## መስራች አባል

በሰሜን ሊቢያ የሴይሬኔካን ባህር ዳርቻን ይዘው ስምንት መቶ ሜትር አካባቢ እንደተጓዙ ግዙፍ ቋጥኝ ያገኛሉ፡፡ሰማንያ ሜትር ስፋት እና ሀያ ሜትር ቁመት ተሸልሟል፡፡ በአካባቢው ዘዬ ”ሃሁህ ፈቲያህ” ተብሎ ይጠራል፡፡ የካርቦን ዴቲንግ ሳይንሳዊ ትንተና እንደሚያሳየው ሰዎች በትንሹ ለመቶ ሺህ አመታት በአካባቢው ኖረዋል፡፡ በቦታው ከተገኙ ቅርሶች መካከል ከዛሬ አርባሺህ እስከ ሰባ ሺህ አመታት በፊት በሚገመት ጊዜ የአካባቢው ሰዎች ይጠቀሙበት የነበረው የአጥንት ዋሽንት ትኩረቴን ሳበው፡፡

በልጅነቴ ይህን ታሪክ ስሰማ አባቴን ”ሙዚቃ ነበራቸው ማለት ነው?” ስል ጠየቅሁት፡፡ አባቴ በጥያቄዬ ፈገግ አለ፡፡

”እንዴታ! እንደማንኛውም ማህበረሰብ!”አለኝ፡፡
አሜሪካዊው አባቴ በሃሁህ ፈቲያህ የመጀመሪውን ቁፋሮ ያካሄደ የታሪክ ተመራማሪ ነው፡፡

ክቡራትና ክቡራን የዚህ አመት የአለም ቴአትር ቀን የአውሮፓ ተወካይ በመሆኔ ታላቅ ክብር እና ደስታ ይሰማኛል፡፡በ1963 ዓ.ም ታላቁ አርተር ሚለር የኒውክለር ጦርነት ስጋት ዓለምን እንደ ግዙፍ ቋጥኝ እንደተጫናት ሲገልጽ እንዲህ ብሎ ነበር፡፡ ”ዲፕሎማሲ እና ፖለቲካ አስፈሪ እና አጭር ብሎም የደከሙ እጆቻችውንን በዘረጉበት ጊዜ እንድጽፍ ብጠየቅ የማስገነዝበው ኪነጥበብ የሰው ልጆችን ህልውና መጠበቅ እንዳለባት ነው፡፡”

የድራማ ትርጉም የተገኘው ከግሪኩ ደራን ቃል ሲሆን ፍቺውም ማድረግ ወይም መከወን ማለት ነው፡፡ እንደ ድራማ ሁሉ የቴአትርም ስርወ-ቃል የግሪኩ ”ቴአትሮን” መመልከቻ ስፍራ የሚል ፍቺን ይዟል፡፡ቴአትሮን ትርዒት የምንመለከትበት ስፍራ ብቻ ሳይሆን ራሳችንን የምናይበት እና ሃሳብ የምንገዛበት ገበያ ነው፡፡

ወጣቱ ፖሊክላይተስ ከ2400 አመታት አስቀድሞ የታላቁን ኤፒዶረስ ቴአትር ቤት ንድፍ አዘጋጅቶ ነበር፡፡ ከቤት ውጪ አራት ሺህ ሰዎችን እንዲያስቀምጥ ተደርጎ የተገነባው ቴአትር ቤት ግርማ ሞገሱ ልዩ ነው፡፡

መሐል መድረክ ላይ የሚለኮስ የክብሪት ድምጽ ለአስራአራት ሺሁም ሰዎች እኩል ይሰማ ነበር፡፡ አይናችሁን ወደ ላይ ስትወረውሩ ከጀርባቸው የሚገኘውን ውብ መልክዓ-ምድር እግረመንገዳችሁን ማየታችሁ በጥንታዊ የግሪክ ቴአትር ቴአትሮች ውስጥ የተለመደ ነው፡፡ ቴአትሩን ከማህበረሰቡ አኗኗር እና ከአማላይ ተፈጥሮ ጋር አብራችሁ ታጣጥማላችሁ፡፡ ተውኔቱ ያለፈ አፈ-ታሪክን በአሁን ውስን ጊዜ የሚመደርክ ቢሆንም እንደተመልካች በመድረኩ አሻግራችሁ የወደፊቱን ተስፋ በተፈጥሮ ውስጥ ትመለከታላችሁ፡፡

በለንደን በድጋሚ የታነጸው የሼክስፒር ግሎብ ቴአትር ቤትም አይናችሁ ተዋናዮችን ብቻ እንዲመለከት አይፈቅድላችሁም፡፡ሰው እንጂ መድረኩም ሆነ አዳራሹ እምብዛም ቦታ የላቸውም፡፡ተዋናይ እና ተመልካች እንደ አለቃ እና ምንዝር አንዱ ላይ አንዱ ታች ሆነው ደረጃ ሳይበላለጡ እኩል ይተያያሉ፤ይነጋገራሉ፤ይሳሳቃሉ፡፡ በየትኛውም አቅጣጫ አንገታችሁን ብታዞሩ ሰዎችን ታገኛላችሁ፡፡ ይህ የመድረክ አሰራር፤ታሪክ በዘመን አይሽሬነታቸው የመዘገባቸውን የሐምሌትን እና የማክቤዝን ንባበ-አእምሮዎች፤ የተዋናዮቹ የደረት ኪስ መታወቂያ ብቻ ሳይሆኑ የሕዝብ መወያያ ሃሳቦች እንዲሆኑ አይነተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

የዘመኑ ጉም ነገሮችን አጥርቶ ለማየት አዳጋች አድርጎብናል፡፡ ከመቼውም ጊዜ በላይ በማይጨበጡ ልብ-ወለድ ታሪኮች ተከበናል፡፡ ዛሬ የተስማማንበት የትኛውም እውነታ ነገ ሊፋረስ ይችላል፡፡ እኛ ከፈለግን የትኛውም ተረት እውነት ሊሆን ይችላል፡፡ እውነት ስምምነት ሆኗል፡፡ ይህ ዘመን አመጣሽ ስምምነት ነው እርስ በርስ ብሎም ከተፈጥሯዊው እውነት ሊለያየን የሚፈልገው፡፡ ዛሬ ተሳክቶለት ተለያይተናል፡፡ የተረገምን ይመስል ህዝቦች ከህዝቦች፣ወንዶች ከሴቶች፣የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ላንደራረስ ተራርቀናል፡፡

የመለያየት እና የመገነጣጠል ውጤቱ ልብን እንዳይረጋጋ ማሸፈቱ ነውና ሰዎች በአንድ ቦታ የማይቀመጡበት ብኩን ዘመን ላይ ደርሰናል፡፡በታሪክ ካስተዋልነው ከየትኛውም ዘመን በላይ ሰዎች ጉዞ ላይ ናቸው፡፡ ገሚሱ በአየር፣ ሌላው በእግሮቹ በዋናም ጭምር ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላው እየተሰደዱ ነው፡፡ አለማችን እየተሰደደች ነው፡፡የሚገርመው ገና ጅማሬያችን መሆኑ ነው፡፡እንደሚታወቀው ሰዎች የተሻለ ህይወት ፍለጋ ቢሰደዱም ምላሹ ድንበሮችን መዝጋት እና ባቢሎንን መገንባት ሆኗል፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ ቸልተኝነት የወቅቱ መገበያያ ገንዘብ ህገ-ወጥ ሀብት ደግሞ የሰው ልጅ ብቸኛ ተስፋ የሆኑበት የጭካኔ ዓለም ኗሪዎች ከሆንን ሰነበትን፡፡ ይህ ጊዜ-አመጣሽ ጭካኔ ቦታ አልበቃ ብሎት ጊዜንም እየተቆጣጠረ ነው፡፡ ዘመናችን ሆን ብሎ ዛሬን ክዷል፡፡ ትኩረቱ የቅርቡ ትላንት እና የቅርቡ ነገ ናቸው፡፡

እኔ ሁለቱም ስለሌሉኝ ተገድጄ ገበያ መውጣት ሊኖርብኝ ነው፡፡ እናም የሚቀጥለውን ለማየት ጓጉቼ ገዛሁት፡፡ ምን ዋጋ አለው? የጥንት ሚባል ነገር የለውም፡፡ የጥንቱ ነገር ሁሉ ለወሬ ነጋሪ እንኳ እንዳይተርፍ ተደርጎ ያለ ርዝራዥ ወድሟል፡፡

ብዙዎች ቴአትር ይህን ያገጠጠ ሐቅ መቀየር እንደማይችል ያምናሉ፡፡ቴአትር ከመነሻው ሰዎች ተሰባስበው ማህበረሰብ የሚፈጥሩበት ቦታ እንደመሆኑ "ስደተኛ" ብዬ ቃሉን ለመጥራት

እገደዳለሁ፡፡ ቴአትር ሰዎች ከተለያየ ቦታ ተሰደው አንድ ስርዓት የሚፈጥሩበት ደስ የሚል አለም ነው፡፡ ሁሉም ቴአትሮች በመጠናቸው የመጀመሪያዎቹን የሰው ልጆች ቁጥር ከሃምሳ እስከ አስራ አራት ሺ.ህ ነፍሶች ይወክላሉ፤ከበረሃ ሲራራ ግመል ነጂዎች እስከ ሶስተኛዋ ጥንታዊት አቴንስ ያሉትን፡፡

ቴአትር አሁናዊ ጥበብ እንደመሆኑ የዘመኑን የጊዜ አመለካከት አይቀበልም፡፡ ምንጊዜም የአሁኗ ቅጽበት ናት የቴአትር ርዕሰጉዳይ! የርዕሰጉዳዩ ውስጣዊ ፍቺ ግን በተዋናዩ እና በተመልካቹ የጋራ ትወናዊ መግባባት ይወሰናል፡፡ ያለተዋናዩ ድርጊት ተመልካቹ ሊያምን እንደማይችለው ያለተመልካቹ እምነትም ቴአትሩ ምሉዕ ሊሆን አይችልም፡፡ በቴአትሩ ውስጥ በተመሳሳይ ጊዜ እንስቃለን፤እኩል እንተነፍሳለን፡፡ አልያም እኩል በአስደንጋጭ ዝምታ እንዋጣለን፤፡ ያቺ የጋራ ቅጽበት ናት እውነትን እንድንፈልጋት የምትረዳን፡፡ ያቺ ቅጽበት ናት በመሀላችን ያለውን ሰበዝ ልዩነት አጥፍታ የእያንዳንዳችንን ንቃት አሰባስባ ሰው በመሆናችን ያለንን ሰፊ አንድነት መልሳ የምትሰጠን፡፡

በመሆኑም ጊዜው ሊያቆመን አይችልም፡፡ በእያንዳንዱ ምሽት ራሳችንን እንገነባለን፡፡ በየምሽቱ ተዋናይ እና ተመልካች የህብረት ቃልኪዳናቸውን ያድሳሉ፡፡ የበፊቱ ድራማ ዳግም ይከወናል፡፡ ደራሲ ጆን በርገር እንደሚለው "በቴአትር ህይወት ውስጥ በሰመጥን ቁጥር ያጣነው ሰዋዊ ተፈጥሮ ተመልሶ ያብባል" ባላንጣዎቻችን ከራሳችን አለም ነው እየነጠሉን ያሉት፡፡ ዛሬ ዛሬ በየቦታው የማይነገሩ ግን የትም ስፍራ የሚከወኑ፤ በየቦታው ያሉ የተመልካች እና የተዋናይ ታሪኮች አሉ፡፡ መከወኛቸውም የትም ነው! ሰው ያለበት ቦታ ሁሉ፡፡ በትላልቅ ከተሞቻችን ያሉ ኦፔራ ቤቶች፣ ግዙፍ የቴአትር አዳራሾች፣ የስደተኛ መጠለያ ካምፖች፣ በሰሜን ሊቢያ ያሉ የስደተኛ ማዕከሎች እና የትም! በየቦታው ሰው ባለበት ሁሉ! በዚህ የአንድነት ቴአትራችን እንደምንጊዜውም ሁሌም አብረን እንቆማለን፡፡

ራሳችንን በኤፒዶረስ ጊዜ ብናገኘውማ ይህን አንድነታችንን በውቡ እና በሰፊው መልክዓ-ምድራችን ላይ ያለገደብ እንጋራው ነበር፡፡ ፍጡር እንደመሆናችን ከተፈጥሮ ተለይተን የትም ልንሔድ አንችልም፡፡ ከመሬት ልናመልጥ እንደማንችለው ሁሉ!

በሼክስፒር ግሎብ ብንገናኝ እንደ መንጋ አጨብጭቦ መሔድ ብቻ ሳይሆን ለእያንዳንዳችን የየግል ጥያቄ ቀርቦልን እንወያይ ነበር፡፡ከአርባ ሺ.ህ አመት በፊት የሴይሬኔካኖችን ዋሻንት ተጫውተንበት ቢሆን ኖሮ ያለፈው ትላንት የዛሬው አሁን ፈጽሞ ሊነጣጣሉ እንደማይችሉ የሰው ልጅ ማህበራዊ መስተጋብርም፣ ሰብዓዊ ሰንሰለትም በጨካኞች እና በግብታዊ መሪዎች እንደማይበጠስም እናውቃለን፡፡

## የሲሞን ማክበርኒ አጭር ግለታሪክ

እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1957 ዓ.ም በኬምብሪጅሻየር የተወለደው ሲሞን ማክበርኒ እንግሊዛዊ ተዋናይ ጸሐፌ-ተውኔት እና መራሔ-ተውኔት ነው፡፡ የእንግሊዝኛ ስነ-ጽሁፍ ትምህርቱን *በኬምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ* ከተከታተለ በኋላ ወደ ፓሪስ አምርቶ የቴአትር ትወናን *በሌኮል ኣንተርናሲዮናል ደ ቴአትር ዣኮ ሌኮ* ለመማር ችሏል፡፡ ከፈረንሳይ መልስ በ1983 ዓ.ም *ቴአትር ዴ ኮምሊሴቴ* የተሰኘ ቡድን ከሙያ አጋሮቹ ጋር በመመስረት የተማረውን ወደ ተግባር ቀይሯል፡፡

ድርጅቱ ስመጥር ከሆነባቸው የኪነ-ጥበብ ስራዎች መካከል *ኒሞነክ(1999)*፣ *ዘ ኤለፋንት ቫኒሽስ (2003)*፣ *ኤ ዶግስ ኸርት(2010) እና ዘ ማስተር ኤንድ ማርጋሪታ(2011)* የተሰኙ ተውኔቶችን በአዘጋጅነት አመድርኳል፡፡ በተጨማሪም ስለ አንድ እንግሊዛዊ የሒሳብ ሊቅ እና እና ህንዳዊ ሳይንቲስት የስራ ጥምረት የሚያወሳውን *ኤ ዲስአፒሪንግ ነምበር* የተሰኘ ተውኔት በ2007 ዓ.ም ጽፎ አዘጋጅቷል፡፡ ተውኔቱ በተለያዩ የዓለማችን ሀገራት ተዟዙሮ ለመታየት በቅቷል፡፡ ከሁለት ዓመት በኃላ በጃፓናዊው ጸሐፌ-ተውኔት *ጁኒቺሮ ታኒዛኪ* ጽሁፍ ላይ መሰረት ተደርጎ የተሰራውን *ሹንኪን* ቴአትር አዘጋጅቷል፡፡

የኮምሊሲቴ ቴአትር ድርጅት በማክበርኒ ምሁራዊ እና ተግባራዊ የቴአትር እውቀት የተቃኘ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ድርጅቱ ቅኔያዊ ቃለ-ተውኔትን ከተጨባጭ እና ምስል ከሳች ድርጊቶች ጋር በሚያዛምደው የአዘገጃጀት ስልቱ ይታወቃል፡፡

ማክበርኒ አሻሽሎ በሰራው *ዘ ኮኬዥን ቾክ ሰርክል* የ1998 *የሎረንስ ኦሊቪየር አዋርድ ቤስት ኬሮግራፊ* አሸናፊ ሲሆን *የክሪቲክስ ሰርክል ቴአትር አዋርድን* ለሁለት ጊዜያት (1997፣2007) ዓ.ም *በኒሞኒክ* እና *ዲስአፒሪንግ ነምበር* ስራዎቹ ድል ሲቀዳጅ፣ በ2005 ደግሞ *የብሪትሽ ኢምፓየር ኦርደር ኦፍ ኦፊሰር ማዕረግን* አግኝቷል፡፡ ከቴአትር ሙያው በተጨማሪ ማክበርኒ የቴሌቪዥን ድራማ እና የፊልም ጸሐፊ እንዲሁም ተዋናይ ሆኖ እየሰራ ይገኛል፡፡

**ተርጓሚ - ምንያህል ተሾመ ቸሩ/** Translation : Menyahel Teshome Cheru

**የቴአትር *መምህር*፣ ጸሐፊና ተዋናይ/** Lecturer, Theater Practitioner

**ኢትዮጵያ/** Ethiopia